# <u>በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ (በሐምሌ 5፣ 2001) በሚነሶታ በግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ የፅሁፍ ንግግር የተሰጠ አስተያየት</u>

በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ("ከወያኔ ዘረኛ እምነቶችና ድርጊቶች ምን እየተማርን ነው።የዘረኛነት አደጋ ለመታገል ምን ማድረግ እንችላለን?") በሚል ርዕስ ለንባብ የበቃው ፅሁፍ አስተያየት ከመስጠቴ በፊት ትንሽ ምን ማድረግ እንዳለብን በሚጠቁም ሃሳብ ብጀምር አንባቢን አያስከፋም የሚል እምነት አለኝ።

ስላለው መንግስት ክፋትና፣አድላዊነነት እንዲሁም ዘረኝነት ለኢትዮጵያ ህዝብ መንገር ማለት ስለ እንቁላል ለደሮ ማስተማር ይመስላል። ምክንያቱም ከቃላት በላይ ስርአቱ የፈጠረውን ችግር ህዝቡ በቀጥታ ገፈት ቀማሽ በመሆኑ ከማንም ፖሊተከኛ ነኝ ከሚለው የበለጠ ይረደዋል፣ ይገበዋል። ባለፉት 18 አመታት የዚህን ስርአት ማንነት በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ስላየነው የተቃዋሚውን ትኩረት በዋናነት የተሻለ ስርአት እንዴት እኛ ኢትዮጵያውያን እንደምንተክልና ከድህነት እንዴት እንደምንላቀቅ እንዲሁም አንድነታችን እንዴት እንደምንጠብቅ መንገዱ ቢያሳዩን ትግሉ የበለጠ ትርጉም ይኖረዋል፣ ብሎም ውጤታማ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ይህን ያልኩበት ምክንያት የትግሉ ሚዛን ወደ ማውገዝና ርግማን ያጋደለ ስለሆነና ይህንኑም የትም ስለማያደርሰን ነው። ደርግ የዘውዱን ስርአት እየወቀሰ እድሜን እንደጨረሰ ሁሉ አሁንም እኛ ስላለው መንግስት ብቻ እያወራን ያለፈውን ስህተት እንዳንደግም መጠንቀቁ ይበጃል ለማለት ነው።

ባገር ቤት ይሁን በዲያስፖራ ያሉት የፖለቲካ መሪዎች ላገርና ለህዝብ የሚበጅ ነገር ትተው ለጊዜው በሚጠቅማቸውና በሚያተርፍላቸው ብቻ ተጠምደው ይገኛሉ። ያለውን ስርአት የወለደው የዘር አስተሳሰብ በሱ ብቻ አልተወሰነም። ተቃዋሚ ነኝ የሚል ወገንም በበሽታው እንደተለከፈ ግልፅ ነው። ወያኔ በዘር ፖለቲካ ነው ወደ ስልጣን የመጣውና እኛም እሱ የሄደበት መንገድ ነው መከተል ያለብን የሚል ፈሊጥ በተቃዋሚው ጎራ ሚዛን የደፋ አስተሳሰብ እየሆነ መጥተዋል።እንዲያውም ባንዳንድ መገናኛ ብዙሃን (በነፃነት ለኢትዮጵያ) "አማራ ባማራነቱ ቢደራጅ ክፋቱ ምንድነው?" ተብሎ በተከታታይ ውይይት ተካሂዶበታል። እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ ጤነኛ አእምሮ ያፈለቀው ሳይሆን ምሬት፣ ቁጭትንና ጥላቻ የፈጠረው ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። እና ለወያኔ አላማ ተገዢ ለመሆን መንገዱ እየጠረግን መሆናችን መታወቅ አለበት። ፍፁም እንደ ሞተ አሳም የወንዙን ፍሰት ተከትለን እየወርድን መሆናችን መሳት የለብንም።

ለሁሉ ኢትዮጵያዊ ወገኔ የማሳስበው ነገር ቢኖር በዘር የሚታሰብ ፖሊቲካ ውጤቱ "አጃን ወቅጠው ቢዘሩት ተመልሶ ወደ ዘሩ ገባ" አይነት ነው የሚሆነው። ሌላው መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ትኩረታችን ስርአትን በመቀየር ብቻ ሳይሆን በሚመጣውንም እጅግ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገን ለማሳሰብ እወዳለሁ። ያለውን ስርአት ያወገዘና የረገመ ሁሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ በጎ ነገር ይመኛል ማለት አይደለም። የራሱ ጥቅምና ስልጣን የሚገደው ሞልተዋል። እንደ ዜጋ በስራ የዋለው ከፋፋይ ፖሊሲ ካገራችን ለመንቀልና ለውደፊትም ተመሳሳይ ፍልስፍና በመከተል በድጋሚ ለራሳቸው ጥቅምና

ፍላጎት የጎሳ ስርአት መልሰው ለማዋቀር ለሚተጉ/ለሚከጅሉ ዜጎች ሃሳባቸውን ሳያንሳራራ መቅጨትና ማምከን የዘወትር ስራችን መሆን እንዳለበትም መዘንጋት የለብንም።

<u>የደጋፊን ልብ ለማግኘት የተደረገ ዲስኩር፡</u>

የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ፅሁፍ የሚጀምረው በራሳቸው ገጠመኝ ሁኖ በሰኔ ወር 2005(በፈረንጅ አቆጣጠር) በወያኔ ሰኩሪቲ የደረሰባቸው ድብደባ፣ ግፍና በደል ምን ያህል ስብእናቸው ወደ የማይወዱትና የሚቃወሙት የዘረኝነት ጎራ እንደገፋቸው አምርረው እንዲህ ሲሉ በብዕራቸው (በገጽ 2-አንቀጽ-4፣-መስመር 1) ይገልጹታል። “ወደ ደብዳቢዎቼ ስመለስ ግማሽ ፊቴን በሰደፍ አፍርሰው ኮማ ውስጥ ጨምረውኝ በጭቃ እጨቀየው የፖሊስ ጣቢያው መሬት ላይ ጥለውኝ ሄዱ።” በመቀጠል ይህንን ድርጊት የተፈጸመው መቀጣጫ እንዲሆን በብዙ መቶዎች እስረኞች ፊት እንደተደረገ ፅሁፉ ይናገራል።

የዚህ ጽሁፍ መንፈስ ስናየው ያለው መንግስት ዘርን መሰረት በማድረግ እየመረጠ እንደሚያሰቃይና እርስዎም በዚሁ የተነሳ የዚሁ ክስተት ግዳይ እንደሆኑና ባማራነታቸው ምክንያት ይህንን በደል እንደደረሰብዎ እንጂ እንደ እርስዎ አይነት ማለትም በተቃዋሚ ጎራ ተሰልፈው መከራና ስቃይ የተቀበሉ ትግርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያንና ሌሎች እንዳሉ ግን ጭራሽ አይገልፅም። <u>ግልጽ ለማድረግ ለምን በእርስዎ የደረሰ በደል ገለፁ አይደለም። የኔ ጥያቄ “**በሁላችን ኢትዮጵያውያን የደረሰ ነው፣ በኔ የተለየ ነገር አልተደረገም**” መባል ነበረበት። ለምን እንደዚህ እንዳልተባለ ግን ግልፅ ነው። ወያኔ ለድል የበቃው ህዝብን የሚያስቆጣ ነገሮችን እየሰበከ ስለሆነ እኔም እንደነሱ ባደርግ የደጋፊን ልብ አገኛለሁ ከሚል የመነጨ እንጂ ሌላ ምስጢር የለውም።</u> ያ ባይሆን እነ ዶ/ር ሃይሉ አርአያና ሌሎች በስም የማናውቃቸው የትግራይ ወገኖች የርስዎ እጣ ፋንታ የደረሰባቸውም መሆኑን አሳምረው ያውቃሉ። ይህ መንግስት በስልጣኑ የመጣ ከትግራይ ይሁን ከወላይታ ምህረት እንሌለው እርስዎም አይስቱትም እኛም በሚገባ እናውቃለን። ሌላው ቀርቶ ለነ ስዩ ይዞ ለ6 አመታት ያለምንም በቂ ማስረጃ ያስቃየና ያንጋላታ መንግስት ነው። በተጨማሪም ከሱ ጋር የነበሩ እንደነ ገብሩ አስራትና ሌሎች ያለ ደመወዝና ጡረታ የሚያባርር ርህራሄ የሌለው ስርአት እኮ ነው። እና በርስዎ የደረሰ ነገር በብዙ ኢትዮጵያዊ የተፈፀመ እንጂ የተለየ ነገር የለውም ለማለት ነው።

የዚህ ፅሁፍ መልእክት አንድ ነገር እንድል አስታወሰኝ። በደርግ ግዜ ማለትም በ1976 ዓ.ም በብዛት ከትግራይ ተ. ሓ ህ. ት እየተባለ ብዙ ሰው ይታሰር ነበር። ሌላው ሳይቀር የመቀሌ ከንቲባ እንካን ከመሃል አገር መጥቶ ከተማዋን ያስተዳደረበት ግዜ ነበረ። እና በእስረኞች ላይ የነበረው ምርመራና ስቃይ በቃላት ለማስቀመጥ ይከብዳል። የትግራይ እስረኞች ለምርመራ ቀርበው “ምንም የለንም” ሲሉ “እሳ ባህር ገብቶ ውሃ አልቀምስኩም ይላል እንዴ? ትግራይ ሁነህ እንዴት ተ ሓ ህ ት አይደለሁም ትላለህ?” እየተባለ ነበር ቁም ስቅሉን ሲያሳዩት የነበረው። የዚህ ክፉ ስራ መሃንዲስ ደርግ ነበር እንጂ አማራ እንዳልነበረ ሁላችን እናውቃለን። እውነቱ ይህ ሁኖ በአቶ አንዳርጋቸው አባባል ግን ደርግ የበደለው ትግራዩን ብቻ ነበረ አማራው ምንም አልሆነም ወይም

አልተነካም ወደሚል ድምዳሜ ሊወስደን ነው። የአድማጭን ስሜት በመቀስቀስ የበለጠ በመሃላችን የጥላቻ ግንብ ለማቆም የቀረበ እንጂ የተለየ አላማ የለውም።

<u>ጥርስን የሚያስነክስ ንግግር፡</u>

በገጽ 3፣ አንቀጽ 3፣ መስመር 3 “ልብ በሉ ስልጣን በኛ ወያኔዎች እጅ ነው አይሉም። በኛ በትግሬዎች እጅ ነው የሚሉት።” እኔ የምለው እነሱ ስላሉ ያ ህዝብ በሙሉ ወከሉ ማለት ነው እንዴ? አዎ እነሱማ የስልጣን እድሜያቸውን ለመቀጠል የማይቀላምዱት የለም። የያዙት ጉዳይ የትግራይ ህዝብ አድርገው ለማቅረብ የዘወትር ስራቸው ነው። ይህ ለማደናገር የሚጠቀሙበት ዘዴ መሆኑን ለማንም የተሰወረ አይደለም። ምርቱ ከግርዱ የመለየቱ ሃላፊነት ያለው እኮ የተሻለ ላገሬ አመጣለሁ ብሎ በሚታገልና ሃላፊነት በሚሰማው ወገን እንጂ ከማንም ሊሆን አይችልም። እነሱ ስላቅራሩ፣ ስለፎከሩና ስለወንድነታቸው ብዙ ስለተናገሩ የሚያስጨንቅ የለውም። ለምን? ባንድ አካባቢ የሚኖርና አንድ የሆነ ህዝብ ልዩነት እንደሌለው በሚገባ ስለምናውቅ።እነሱ ለግል ጉዳያቸውና ሆን ብለው የሚያፈሱትን ሁሉ እየለቀምን ባቅማዳችን የምንቻጥር ከሆነና በተራችን ያንን የምንዘራ ከሆነ እነሱና እኛ የሚለየን ምን ሊሆን እንደሚችል አይገባኝም። እኛ ወደነሱ አለም ላለመግባት መታገል እንጂ እነሱ በፎከሩ ቁጥር የምንናደድና እንደነሱ ለመሆን የሚነሽጠን ከሆነማ፣ የኛ መሻል ከነሱ በምንድነው የምናስረግጠው? እና አሁንም የደጋፊን ልብ አስቆጥቶ ለግል ጉዳይ ለማዋል የቀረበ ሃሳብ እንጂ በጎ ለምንመኝላት አገራችን ጠቃሚነት ኑሮት የተነገረ አይደለም ባይ ነኝ።

<u>*ፀሃፊው ዘረኛነትን ሲተናነቃቸው፡*</u>

በገጽ 5፣ አንቀጽ 4፣ መስመር 3 *“ይህ መሰሪ የሆነ የወያኔ ድርጊት የማታ ማታ የሚኖረው አስከፊ መዘዝ በሚገባ ተርድተው በግዜ ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ እየበከለ ያለውን የትግራይና...በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን አይን ያወጣ በደል...ዘረፋ መቃወም ያለባቸው በዋንኛነት እራሳቸው የትግራይ ተወላጆች ናቸው።”* ይልና <u>የኛና፣ የእነሱ</u> የሚለው አስተሳሰብ በሚከተለው መስመር ሲያጠናክሩት እናያለን፡

*አንቀጽ [5] መስመር 1፣ ሌሎቻችን...ለራሳችን ክብር ደህንነት ቅድሚያ ሰጥተን ወያኔ እኛን አዋርዶና ዘረኛ በሆነ አላማው መግዛት እንደማይችል ማሳየት አለብን ይላል።ወያኔን በግምባር ቀደም መታገል ያለባቸው የትግራይ ተወላጆች ናቸው ምክንያቱም ወያኔ ያደገበትና ብሎም ወደ መንበረ ስልጣን የወጣው ከትግራይ ተነስቶ ስለሆነ እንዲሁም አሁን አገሪቱን ወደአልሆነ መንገድ የሚውስዱን ያሉ ከትግራይ የወጡ ስለሆነ ይህንን ስርአት ለማስወገድ በሚደረግ ወሳኝ ትግል የአንበሳ ድርሻ የሚይዙት እነሱ መሆን አለባቸው የሚል ነው። የመጀመሪያ ጥያቄ ትግራይ ኢትዮጵያ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ሌላው እንግዲህ ይህ ማለት ደርግ በመሃል አገር ነው የተመሰረተውና የመሃል አገር ሰዎች ደርግን ለመጣል በቅድሚያ መሰለፍ ነበረባቸው ቢባል እውነት ነበረ ማለት ነው በፀሃፊው አባባል። እንዲህ አይነቱ ትንተና ከእውንታ ጋር የሚቃረን ነው።ዘረኝነትን በጥብቅ እቃወማለሁ ከሚል የፖለቲካ ድርጅት መሪ፣አገራችን ከወደቀችበት አዘቅት አነሳለሁ ከሚል ሰው፣ ከአንደበታቸው የጎሰኝነት መንገድ የገሃነም መንገድ መሆኑን በነገሩን ሊቅ ራሳቸው ሲያፈርሱት ማየቱና መስማቱ ያስገርማል። እኛና፣ እነሱ የሚል መንፈስ መስበክ*

ከጀመሩ እንግዲህ መልሳችን የሚሆነው ምነው ስምዎ ከአንዳርጋቸው ወደ በትናቸው ተለወጠ ነው። ያለውም ስርአት እኮ በብሄረሰብ መብት ሰበብ አድርጎ ነው ወደማይሆነው መንገድ የሚወስደን ያለው። የጠላነውም ለዛ መሰለኝ። እርስዎስ ታድያ ከሱ በምን ተለዩ?

የፀሃፊው አባባል ስህተትነት ካለፈው ታሪካችን ጋር በማያያዝ ትንሽ ልበል። በኤርትራና ትግራይ ላመታት የዘለቀው ጦርነት ብዙ ጉዳት በማድረሱ ይህን የሚሰራውና የችግሩ ምንጭ አማራ ስለሆነ እኛን መግዛት የለበትም የሚል ፕሮፖጋንዳ ለህዝቡ መነገር ተጀመረ። በኤርትራ ህዝቡ ምን እንዳለ ባላውቅም በትግራይ ግን “አማራ ቢገዛ ምን ችግር አለው? ወንድማችን አይደለም ወይ? ግዜ ሲሰጥ ከእኛ ገዢ ይወጣል ሌላ ግዜ ደግሞ ከሱ” የሚል ነበር። የወያኔ መሪዎች ግን በዚሁ እውነተኛ መልስ ደስተኞች አልነበሩም። የእነሱ ፍላጎት የነበረው ያሉትን የሚደግምና አሜን ብሎ የሚቀበል ነበር። እውነቱ ግን አማራ ሳይሆን ደርግ ነበር ለሁላችን ሲገርፈን የነበረው። በነሱ የወረደው መከራ ባማራው መፈጸሙ አይነገርም ነበር። ምክንያቱም የፖለቲካ ድርጅቶቹ የራሳቸው አላማ ስለነበራቸው የሚነግዱበት ብቻ ነበር ወደ ህዝቡ ጆሮ እንዲደርስ የሚያደርጉት። እውነቱን ግን ለምሳሌ በጎንደር እንካ የደረሰው አስከፊ ጭፍጨፋ ብናይ ከ2000 (ከሁለት ሺ) በላይ በቀይ ሽብር በሻለቃ መላኩ (ባማራው ወይም በጎንደሬው) አማካይነት ማለቁ በደንብ ይታወቃል። ይህ በወሬ ሳይሆን እኔው ራሴ በጎንደር በአታ ወህኒ ቤት በነበርኩበት ስዓት ባጋጣሚ የመላኩ አጃቢ ታስሮ ስለነበረ በነበረን መቀራረብ የነገረኝ ነው። እንግዲህ ጎንደሬ ሁኖ ለጎንደር አልራራም። ይህ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ያንተ ዘር ስለሆነ ደግ ነገር ይሰራልሃል የሌላ ዘር ከሆነ ግን ባንተ ጥሩ አይሆንም የሚለው አባዜ ውድቅ ያደርገዋል። ሻዕብያና ወያኔ የደርግ ስርኣት ከተወገደ በሃላ ህዝቡ ከሰማይ መና እንደሚወርድለት ነበር ሲሰብኩ የነበረው። ውጤቱ ግን ያው እንደምናየው ነው። ፍትህና መልካም አስተዳደር ከዘር ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው ባይናችን እያየን ነው። እንዲያውም ለበለጠ ጭቆናና የመብት ረገጣ ምቹ መንገድ እንደፈጠረ ሁላችን በተጨባጭ የምናየው ክስተት ነው። ይህንን ሁሉ የዳሰስኩት የአቶ አንዳርጋቸው አባባል ከሻዕቢያና ወያኔ ከሚሉት ከነበረ ጋር ስለተመሳሰለብኝ ነው።ታሪክ ራሱ ይደግማል ሆነና መሰለኝ ያለፈው ስህተት በመድገም የተለየ ውጤት የሚገኝ ይመስል አሁንም በዛ ጎዳና እንድንሄድ በግንቦት 7 የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች እየተገፋን ነው።የሚገርመው ነኔ አገር እንመራለን ከሚል አንደበት ሲነገር ነው የሚያሳዝነው። ተራው የኔ ብጤ አይነቱ አሁን እንደርስዎ ቢያስብ ወይም ቢያምን ግድ የለኝም። መሪነት ማለት እኮ መትፋት የሚገባህን እየዋጥክ፣ እተካዋለሁ ብለህ ከምታስበው ድርጅት በልጠህ መገኘት እንጂ ያንድ ወቅት ፍፃሜ ወደ እልህና ጥላቻ የሚወስደን ከሆነ አሁንም ችግራችን ቀጣይ ነው ማለት ነው።

<u>ሃቁ ሌላ ነው፥</u>

ፀሃፊው የስርአቱን ደጋፊዎች የሚሉትን ልክ የብዙሃኑ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል እንዲህ በማለት፣ “ይህን የወያኔ አደገኛ አመለካከትና ድርጊት የሚኮንኑትን የሌሎች ዘውጌ ማህበረሰብ አባላት በጸረ ትግሬነት መኮነኑን ትተው በቅድሚያ ማውገዝ የሚገባቸው የወያኔን ፋሽስቶችንና ዘራፊዎችን ሊሆን ይገባል” (ገፅ 5፣ አንቀጽ 4፣ መስመር 9) ።

ወያኔ ስለተወገዘ የሚከፋው ቢኖር ያው የነሱ አባል ወይም ደጋፊ ስለሆነ ምን ማድረግ ይቻላል? ከዛ ውጭ ያለው ማህበረሰብ ግን ያለው ስር አት ስለተወገዘ የከፋው የለም። ይልቁንስ የሌለውን አለ ከማለትና እንዲሁም በተቃራኒ ያለው እውንታ እንደሌለ በመቁጠር ከመግለጽ ወደ ኃላ ማለት ትርፉ ማነስ ነው። ፀሃፊው ሆን ብለው ለማንሳት ያልፈለጉት ቁም ነገር ግን የትግራይን ህዝብ ካለው ሰርአት (ፀሃፊውም እኛና እነሱ ብለው እንዳስቀመጡት) አጣምሮ የማየት ምን ያህል ባንድ አገር ልጆች የልዩነት አምባ እንደፈጠረ ነው። አብረን ላገራችን እንዳንታገል ነቀርሳ የሆነብን ይህንኑ አስተሳብ ነው።ህዝብን ከድርጅት ጋር ደምሮ ተጠያቂ የማድረግ ዝንባሌ በተቃዋሚው ጎራ የነገሰ መሆኑን ይታወቃል። ይህም ሁኖ የትግራይ ተቃዋሚ ስርአቱን ከመታገል አልቦዘነም። ምናልባት ከፀሃፊው የፖለቲካ ድርጅት ጋር የሌለ ይሆናል እንጅ አሉ ከሚባሉ ድርጅቶች ሁኖ ድርሻውን እየተወጣ መሆኑን ግልፅ ነው። ለምሳሌ በቅንጅትና፣ በሌሎች መድረኮች ተሰልፎ ይህንን ስርአት እየተታተገለ ይገኛል። በርግጥ ሁላችን ኢትዮጵያውያን የሚገባንን ያህል ለትግሉ መጎልበት ስንቀሳቀስ አንታይም። ይህም ደግሞ የሁላችን ችግር እንጂ ላንድ ወገን ብቻ በዚሁ ጉዳይ የሚወቀስበት ምክንያት ትክክል ሊሆን አይችልም። እና ፀሃፊው አሁንም ለሚፈልጉት የግል ጉዳይ ብቻ የሚያገለግል ሐረግ እየመዘዙ ከመንገር አጠቃላይ ያለው ችግር ምን እንደሆነ ቢያቀርቡ ኑሮ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ለማየት ባስቻለ ነበር፣ በስብሰባው የተገኘው ወገንም ሙሉ እውነትን ሰንቆ ለመሄድና የተሻለ ግንዛቤም ለመጨበጥ ይረዳው ነበር።

<u>ባንድ ራስ ሁለት ምላስ፡</u>

ከጅምሩ ጀምሮ መባል የነበረበት ጉዳይ ወደ መጨረሻ አካባቢ ዘረኛነት እነደ ማያዋጣ ፀሃፊው በግልጽ ነው ያስቀመጡት፡ *“ከወያኔ ዘረኛ አካሂድ መማር የሚገባን የወያኔ ዘረኛነት ባስመረረን ቁጥር እያንዳንዳችን የራሳችንን በዘር ላይ የተመሰረተ አጥር በመስራት ችግሩን ልንፈታው የማንችል መሆኑን ነው” ይላል (ገጽ 6፣ አንቀጽ 2፣ መስመር 1)* ። አንዱን ወገን የበለጠ ድርሻ እንዲነረው የሚያደርግ ሳይሆን ሁላችን ባንድነት ቁመን ነው ይህን ስርአት መታገል ያለብን የሚለው የሚያስረግጥ ነው። እንግዲህ ከቅድሙ አባባል ማለትም ለትግራይ ሰዎች ካባድ ሃላፊነት የሰጠ ብዕርና አንደበት በዚሁ ፈረሰ። ከባድ ሃላፊነቱም የጋራ ሆነ፣ ሉታውም በአዎንታ ተደመሰሰ ማለት ነው። ከላይ ከተቀመጠው ሃሳብ በሚቀጥለው ሲያጠናክሩ (ገጽ 7፣ አንቀጽ 1] እንዲህ ይላሉ፡
የሁሉም ብሄር መብት መጠብቅና ማስከበር የዘረኝነትን በሽታ መፈወሻ እንደሆነ ያሰምራሉ። ከዚሁ ገጽ ሳንወጣ (በአንቀጽ 4) በየብሄራቸው-ጉዳይ-ተጠምደው-ያሉ ግለሰቦችና ቡድኖች በዋናነት ወደ አገራዊ ጉዳይ እንዲገቡ ማድረግና በዚሁ መሰረት የወያኔ ግርድፍ ፖለቲካ አሽቀንጥሮ ለመጣል ፍቱን መሳርያ መሆኑን ጽሁፉ ይተነትናል።
ይህ መልዕክትም በቃሉ እንከን የለውም። ችግሩ ግን ይህን ጥሩ ሃሳብ ወደ ሚበላ ፍሬ ለመቀየር ግን <u>እነሱና እኛ</u> ከሚለው ሩቅ ከማይኻዝ የፖሊቲካ ፋሽን በመውጣት ወደ እውነተኛ የዳገት መንገድ መውጣትን ይጠይቃል። ባገራችን ምድር የማይጠቅመን ስርአት ከየትም ይምጣ በጋራ እናስወግደው ነው መባል ያለበት። መፍትሄው ችግር ለመቅረፍ ባንድነት ስንሰለፍ፣ ጥሩ ሲገኝ ደግሞ ለጋራ ስንካፈል ነው። ይህንን በስራ ካዋልነው የችግራችን ምንጮች በሙሉ ለዘላለም ተደፈኑ ማለት ነው።

ኃይለ ደስታ